

# ሰሎሞን

* ንጉስ ዳዊት ከሞተ በኋላ ልጁ ሰሎሞን በእርሱ ቦታ የእስራኤል ንጉስ ሆነ።  እግዚአብሔር በአንድ ሌሊት በሕልም "እንድሰጥህ የምትፈልገውን ነገር ለምነኝ።"አለው።

* ሰሎሞን  ሀብት፣ ረጅም እድሜ፣ በጠላቶች ላይ ድል እንዲሰጠው መለመን ይችል ነበር።." ነገር ግን እግዚአብሔርን እንዲህ ሲል ለመነው "ሕዝብህን የማስተዳደርበትንና ክፉውንና መልካሙን መለየት የምችልበትን አስተዋይ ልቦና ስጠኝ።" ብሎ ለመነው።

* እግዚአብሔርም የለመነውን ጥበብ ሰጠው። ሌሎቹንም ያልጠየቃቸውን ነገሮች ማለትም ሀብት፣ ረጅም እድሜ፣ በጠላቶች ላይ ድልን ጨምሮ  ሰጠው።

* ሰሎሞን ስለዛፎች፣ ስለአዕዋፍ፣ ስለአሳዎችና ስለ እንስሳት መናገር ይችል ነበር።  ሌሎች ሰዎች የማያረዷቸውን ነገሮች እርሱ ይረዳ ነበር። ስለዚህም ብዙ ሰዎች እርሱ ሲናገር ለመስማት ከተለያዩ አገሮች ወደኢየሩሳሌም ይመጡ አንድ ጊዜ የሳባ ንግስት እርሱን ለመስማት መጣች።

* አንድ ጊዜ ደግሞ ሁለት ሴቶች አንድ ሕፃን ይዘው ወደእርሱ መጡ። ሁለቱም ሴቶች በሰሎሞን ፊት ልጁን የእኔ እያሉ ተወዛገቡ።   ሰሎሞንም " ልጁን ለሁለት ቁረጡትና ለሁለቱም ሴቶች አካፍሏቸው ብሎ አዘዘ። (እንደእውነቱ ከሆነ ልጁ እንዲቆረጥ አስቦ ሳይሆን ሴቶቹን ለመፈተን ያደረገው ዘዴ ነበር።)" በዚህን ጊዜ እውነተኛይቱ እናት "አይሆንም አትግደሉት፣ ለእርሷ ስጧት!" ብላ ጮኸች። ሰሎሞንም ያኔ እውነተኛይቱ እናት ልጁ እንዲቆረጥ ያልፈለገቸው እናት እንደሆነች ተረዳ። ስለዚህም ልጁን ለእውነተኛይቱ እናት አስረከበ።

* እግዚአብሔር ሰሎሞን  እግዚአብሔር የሚመለክበትን ውብ ቤተመቅደስ እንዲገነባ ፈቀደለት።

* ሰሎሞን ከተለያዩ አገራት የመጡ ሴቶችን በማግባት ትልቅ ስህተት ሰራ። እነኝህ ሴቶች ጣኦት አምላኪዎች ነበሩ። ሰሎሞንም ከእነርሱ የተነሳ ጣኦታትን ማምለክ ጀመረ።  እንደአባቱ ለእግዚአብሔር ታማኝ አልነበረም።

የሰሎሞን ታሪክ በመፅሐፍ ቅዱስ በአንደኛ ነገስት መፅሐፍ ምዕራፍ 3 እና ምዕራፍ 4 ውስጥ ይገኛል።

http://gardenofpraise.com